Roots and wings

# የጥንካሬ እና የጽናት ተምሳሌቷ ሴት!

እና ሌሎችም

ያልተመለሰው የመስማት የተሳናቸው ሴቶች ብሔራዊ አካታችነት ጥያቄ

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የጎለበተ የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ፕሮጀክት




Roots & Wings

ConceptHub ETHIOPIA

Powered by TIKVAH ETHIOPIA

**ኤዲቶሪያል**
ኮንሰፕት ሀብ ኢትዮጵያ

**ኤዲቶሪያል**
ኮንሰፕት ሀብ ኢትዮጵያ

**ጸሐፍያን**
ናትናኤል ሽፈራው
ጋሻው ተሥፋው
ስንሻው ሰገሰ
መሠረት በሰጽ
አርሴማ ማንጸፍሮ
ሀብታሙ ታደሰ

**የመጽሔት ዲዛይን**
ሰሎሞን ሸዋረጋ

**ዲጂታል ህትመት ሥርጨት**
ቲክቫህ ኢትዮጵያ

**Published for:**
Roots and Wings ELIXIR

https://www.rootsandwingsglobal.org/
+251 91 28 01534

**Published by:**
Concepthub Ethiopia |Powered by TIkvah Ethiopia

+251 91 313 4524
https://www.concepthub.net

# ይዘት
# Content




5

ያልተመለሰው የመስማት የተሳናቸው ሴቶች ብሔራዊ አካታችነት ጥያቄ




13

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የጎለበተ የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ፕሮጀክት



20

የጥንካሬ እና የጽናት ተምሳሌቷ
ሴት!

# መልእክት

## ውድ አምባቢያን

ይህ መጽሔት በውስጡ የያዛቸው ታሪኮችና ዘገባዎች እንዲሁ በዘፈቀደ የተሰበሰቡ ሳይሆኑ፣ በታላቅ ጥንቃቄና ግልጽ በሆነ መስፈርት የተመረጡ ናቸው። ለዚህ እትም የሚሆኑ ጽሑፎችን ለማሰባሰብ ባወጣነው ግልጽ የጽሑፍ ውድድር ጥሪ፣ ከየአቅጣጫው በርካታ ተሳታፊዎች ድምፃቸውን ለማሰማት ጥረት አድርገዋል።

ይህ የጽሑፍ ውድድር ለሁሉም ክፍት የነበረ ሲሆን፣ በመጨረሻም ለህትመት የሚበቁ ሥራዎችን ስንመርጥ ሦስት መሠረታዊ መርሆችን ትኩረት አድርገን ነበር።

በመጀመሪያ፤ መስማት የተሳናቸው ወገኖቻችን በራሳቸው ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑና የራሳቸውን ታሪክ በራሳቸው አንደበት እንዲተርኩ ትልቅ ዕድል ሰጥተናል። ይህ ውሳኔያችን "ስለ እኛ ያለ እኛ ተሳትፎ" የሚለውን መርህ በተግባር ለማዋልና ትክክለኛውን ድምፅ ለተደራሲያን ለማድረስ ያለመ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፤ የጋዜጠኞችን ሙያዊ አበርክቶና ሚና አክብረናል። ጋዜጠኞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉና ብዙ ያልተባለላቸውን ጉዳዮች በሙያዊ ብቃት አቀናብረው በማቅረብ፣ የችግሩን ጥልቀትና የመፍትሔውን አቅጣጫ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲያሳዩ ተደርጓል።

በሦስተኛ ደረጃ፤ እስካሁን ካልተነገሩና ከተደበቁ ታሪኮች መካከል ለሰዎች ትልቅ ትምህርትና ተሞክሮ ሊሆኑ የሚችሉ ሥራዎች መዝነው እንዲመረጡ ተደርጓል። እነዚህ ታሪኮች ግለሰባዊ ትግልን ብቻ ሳይሆን፣ ሰፊውን የማኅበረሰብ ግንዛቤ የሚፈትኑና አዲስ እይታን የሚሰጡ ናቸው።

ይህ አሳታፊ የሥራ ሂደት ፕሮጀክቶችንና መርሐ-ግብሮችን አካታች ከማድረግም ባለፈ፣ በዝምታ የታጠሩና ጆሮ ያላገኙ ታሪኮችን በቀላሉ ወደ ሰው ጆሮ የሚያደርሱ ድልድዮች ናቸው። በዚህ መጽሔት ውስጥ የምታገኟቸው ገጾች ሁሉ የእነዚህን ወገኖቻችንን የጽናት፣ የፈጠራና የብቃት ታሪኮች በዝርዝር የሚተርኩ ናቸው።

ይህ መጽሔት የሁላችንንም ግንዛቤ በማስፋት፣ ለተሻለና ለተሟላ አካታችነት መንገድ እንደሚከፍት ተስፋ እናደርጋለን።

መልካም ንባብ!




# ያልተመለሰው የመስማት የተሳናቸው ሴቶች ብሔራዊ አካታችነት ጥያቄ

በጋዜጠኛና መምህር ናትናኤል ሽፈራው

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ምድር ጆሮ ጭው ከሚያደርጉት ጉዳዮች በሴት ላይ የሚፈጸሙ መብት ረገጣ አድሎአዊ አሰራር ጾታዊ ጥቃት የጉልበት ብዝበዛ የሚጠቀሱት ቢሆኑም እነዚህ ድርጊቶች የሚፈጸሙት መስማት የተሳናቸው ላይ ነው ሲባል ድንጋጤውን ጎላ ያደርገዋል በመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰብ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን ደግሞ በወደፊት ሕይወታቸው የማያባራ ጭንቀት ይፈጥርባቸዋል በመሰናክል በእንቅፋት በተዳግሮቶች የተከበበን የሴትነት ሕይወት አልፈው ሃገራቸውን ለማገልገል በተሰናዱበት ሰዓት ተስፋ አስቆራጭ በደል በእህቶቻቸው ሲፈጸም ነገ በኔ ለይም ይደርሳል የሚለው ስሜት ስለሚቆሰቆስባቸው ዛሬም ድረስ መስማት የተሳናቸው እህቶቻችን ተምረው የማያድጉ ሰርተው የማይለወጡ የሚመስላቸው ኃላቀር እሳቤን የሚያራምዱ በርካታ ግለሰቦችና ተቋማት አሉ መስማት የተሳናቸው ባቅራቢያቸው ባለ ት/ቤት የመማር መብት እያላቸው ከሩቅ ቦታ ለመምጣት ይገደዳሉ ይህ ደግሞ ወላጅን ላልተፈለገ ወጪ የሚዳርግ ተማሪዎቹ በትራንስፖርት በመመላለስ የጥናት ጊዜያቸው እንዲባክን በር የሚከፍት ለትራንስፖርት ወጪ መክፈል ለማይችሉት ደግሞ በእግር ጉዞ በመመላለስ አካላቸውና አእምሯቸው ደካክሞ ባግባቡ እንዳይማሩ የሚያስደርግ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው። ታመው እንኳ የሕክምና አገልግሎት ቢፈልጉ አብዛኞቹ ባለሙያዎች ቋንቋውን ሰለማይችሉ በተግባቦት ክፍተት ለተደራራቢ በሽታዎች ይጋለጣሉ አንዳንዶቹ እህቶቻን አስተርጓሚ ባመጣ ሚስጠሬ ይወጣብኛል በማለት እየተጨነቁ ከሕመማቸው ጋር ይታገላሉ። ከነዚህ አይነቱ ቁስሎች ሳያገግሙ ያገኗትን ሰርተው ተከራይቶ ለመኖር ቤት ቢያፈላልጉ እንኳ መስማት መሳንነታቸው ከችሎታ ማነስ ጋር አያይዘው ምን ሰርታ ልትከፍል ነው በሚል የወረደ አስተሳሰብ ገብተው እንዳይኖሩ ይከለክላሉ። ይህ አካታችነት


የሌለው አግላይ ሁኔታ ደግሞ መስማት የተሳናቸው እህቶቻችን በተለያዩ ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ይገድባቸዋል ዘገባውም ተኮር የሚያደርገው በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ስለሚያጋጥማቸው ፈተናዎ ነው።

መስማት የተሳናቸው ሴቶች በሕዝብ መገልገያ ቦታዎች በትምህርት ስርዓት እና በአካባቢያቸው ስለሚያጋጥማቸው ፈተናዎች ጥያቄ የቀረበላቸው ግለሰቦችና ተቋማት ምን ይላሉ ?

መ/ርት ሕሊና ሳሙኤል “አብዛኛዎቹ የሕክምና ባለሙያዎች ምልክት ቋንቋ ስለማይችሉ በግሌ አስተርጓሚ ከፍዬ በማምጣት የምታከም ቢሆንም ሚስጥሬ ለሶስተኛ ወገን ስለሚወጣብኝ ለከባድ ጫና እዳረጋለው” በማለት ገልጻለች።

መምህሯ አክላም ይህ በኔ ብቻ ሳይሆን በመላ ሃገሪቱ የሚገኙ መስማት የተሳናቸው ዜጎች ካጋጠማቸው ሕመም ለመዳን ሲሉ ግብር ለሚከፍሉት ሃገር ታመው እንኳ በድጋሚ ለምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በመክፈል ለተጨማሪ ወጪ የሚዳረጉ መሆኑ በመግለጽ ሐኪም ብቻ ማወቅ የሚገባው ሚስጥር ለሌላ መውጣቱ ለከባድ ስነ-ልቦና ችግር እንደሚፈጥባቸው በዚህም ምክንያት ራሳቸውን ከማሕበራዊ እንቅስቃሴ እንደሚያገሉ እንዲሁም በተግባቦት ክፍተት የተነሳ አንዳንድ ሃኪሞች ማስታገሻ በመውጋት ተሽሎሻል በማለት እንደሚሸኙ የገለጽች ሲሆን የሕዝብ መገልገያዎቹ መስማት የተሳናቸውን ፍላጉት ባማከለ መልኩ አለመቅረባቸው ገልጻለች።

መስማት የተሳናቸው በሕክምና ተቋማት የሚያጋጥማቸው ችግሮች ለመቅረፍ የአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማሕበር ምን እየሰራ ይገኛል ? የሚል ጥያቄ ለቀረበላቸው የማሕበሩ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ወይንሸት ግርማ ማሕበሩ መስማት የተሳናቸው በጤናው ዘርፍ ምቹ አገልግሎት እንዲያገኙ ጠይቀን በሁሉም የጤና ጣብያዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ



እንዲቀጠር ተፈቅዶ ጉዳዩ ወደ ፐብሊክ ሰርቪስ ፕሮሰስ ለማድረግ በሂደት ላይ መሆኑን በመግለጽ ተስፋ ሰጪ ምላሻቸውን ሰጥተውናል። የተለያዩ ጉዳዮችን ለማስፈጸም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት እስከ ወረዳ ያሉት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት “መስማት የተሳነን በመሆናችን ጉዳያችንን በማቃለል እሱን ጠይቁ እኔ አይመለከተኝም ያ ክፍል ያስተናግዳችሁ” በማለት በቢሮክራሲ እንደሚያጉሏሏቸው በምሬት ገልጸዋል አንድ ስሟ እንዲጠቀስ ያልፈለገች መስማት የተሳናት ተገልጋይ እኔ ዜጋ ነኝ እንደማንኛውም ተገልጋይ በቋንቋዬ አገልግሎት ላገኝ ይገባል እንጂ መስማት ባለመቻሌ ምክንያት ልጉላላ አይገባም በማለት ገልጻለች።

“ከመስማት የተሳናቸው ጋር የሚያግባቡ መንገዶች አስተርጓሚ ብቻ አይደለም” የምትለዋ መ/ርት ሞላሸ ኃይሉ መስማት ባንችልም የከንፈር እንቅስቃሴን አይተን እንደምንግባባ ወይ የምንፈልገውን አገልግሎት በጽሁፍ አስፍረን ሃሳባችንን መግለጽ የምንችል ብንሆንም የነሱን ምላሻቸውን ብንጠብቅ ግን ላለመጻፍ በመሰላቸት በቃ አስተርጓሚ ይዛችሁ ኑ በማለት አስተርጓሚ ማቅረብ የኛ ግዴታ አድርገው እንደሚቆጥሩት አብራራታለች፡ ፡ በእያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለምን የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አልተዘጋጀም ? ለሚለው

openaccessgovernment.org

ጥያቄ ከመልስ ሰጪዎች ውስጥ ለበርካታ አመታት በትርጉም ሙያ ውስጥ ያሳለቸፈችው ምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ሃይማኖት ሽፈራው ሙያው ተገቢውን ትኩረት አላገኘም እስካሁን ድረስ በዘፈቀድ የሚሰራ እንጂ አንደ ሌሎቹ የሙያ አይነቶች የስራ መደብ ፣ የደሞዝ ስኬል ፣ ደረጃ እድገት . . . ወጥቶለት ሳይሆን የሕግ ማዕቀፍ በሌለው ሂደት ውስጥ ሚመደብ በመሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በምን አይነት መመሪያ እንደሚቀጥሩ ውዥምብር ስለሚፈጥርባቸው አስተርጓሚን ላለመቅጠር ይገደዳሉ በዚህም ምክንያት በርካታ አገልግሎት ፈላጊ መስማት የተሳናቸው ወገኖች ላልተገባ እንግልት ይዳረጋሉ በማለት ሙያው ስላለበት ሁኔታ ገልጻለች::

> “ከመስማት የተሳናቸው ጋር የሚያግባቡ መንገዶች አስተርጓሚ ብቻ አይደለም”

ይህ በቸልተኝነት የማይታይ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ሲሆን ሃገራችን መስማት የተሳናቸውን የሚመለከቱ አለም አቀፍ ሕጎች ተቀበለች ቢሆንም የመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰብ ልዩ መብት የሆነውን አስተርጓሚ አለማዘጋጀት ተቀበለቻቸው ሕጎች ሚቃረን ድርጊት በመሆኑ ከወዲሁ አፋጣኝ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል:: “አንዳንድ ነውረኛ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች በየተቋሙ ውስጥ አሉ” የምትለው ስሟ እንዲጠቀስ ያልፈለገች ሌላኛዋ ተገልጋይ መስማት ስለማትችዪ ሁሉንም ፕሮሰስ እኔ ልጨርስልሽና ለሁለታችን ደስ የሚል ምሽት እናሳልፋል በማለት አገልግሎትን በዚህ መንገድ እንሚደልሉ ትናገራለች::

ሙያው ሃገሪቱ ውስጥ ባሉት ፕሮግራሞች ተካቶ መስማት የተሳናቸው ማሕበረሰቦች በሕዝብ መገልገያ ቦታዎች ያለ እንግልት ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ምን ስራዎች ተሰርቷል ? የሚል ጥያቄ የቀረበለት በቅርቡ የተመሰረተው የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ብሔራዊ ማሕበር ምላሽ ሊሰጡ ባለመቻሉ አሰተያታቸውን ማጠናቀር አልተቻለም:: “ችግሩ ከመንግስት አይደለም ከእኛው አስተርጓሚዎች ነው” የምትለዋ ሌላኛዋ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ቅደስት ኃይሉ በ2012 ዓ.ም የወጣው የቋንቋ ፖሊሲ ለምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች መብትና ጥቅም ሊያስከብር የሚችል በትርጉም ሙያው ውስጥ ላሉ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እውቅና የሚሰጥ እንዲሁም የመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰቦችንም ችግር ሊፈታ የሚችል ወርቃማ ዕድል ሆኖ መጥቷል ይሁን እንጂ ለፖሊሲው ዝርዝር መመሪያ የሚያወጣው የዘርፉ ባለሙያዎች እንጂ ፖሊሲውን ያወጣው አካል ባለመሆኑ አስተርጓሚዎች ተባብረው ባለመስራታቸው እስካሁን ፖለሲው ማስፈጸሚያ መመሪያ ሳይወጣለት በዘፈቀድ እየተሰራ ይገኛል በዚህ ምክንያት ተገልጋይ የሆኑ መስማት የተሳናቸው አስተርጓሚ በማጣት ለከፍተኛ እንግልት ይዳረጋሉ በማለት በማለት አስተያየቷን ሰጥታለች::




ከሕዝብ መገልገያ ጋር ተያይዞ ጥያቄ የቀረበላቸው ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች “በየጊዜው ከሚያማርረን መፍትሔ ካልበጀላቸው ጉዳዮች አንዱ የሕዝብ ትራንስፖርት ነው” የምትለዋ መ/ርት አሚራ ሐሰን የት ነው ብዬ ብንጠይቅ መልሳቸውን መስማት ሰለማልችል ሌሎች ሰምተው ወዲያውኑ ይሞሉታል በዚህም ምክንያት አምሸቼ የምገባበት ጊዜያት ብዙ ናቸው በማለት ገልጻለች::

ሌላኛዋ የትራንስፖርት ተጠቃሚ ሆነችው ወጣት ረድኤት

ታሪኩ በተለይ ታክሲ ከሆነ ከባድ ነው ወያላዎቹ የት እንደሚሄድ የሚጠሩት በአፋቸው ስለሆነ የከንፈር እንቅስቃሴን ለመራዳት እንከታተላቸዋለሁ ካልገባኝ ልላ ሰው ለመጠየቅ እሞክራለሁ ይህም አድካሚ ነው ያለችው ትራንስፖርት ተጠቃሚዋ በዚህ ጉዳይ መፍትሄ እንዲገኝለት ሁሌም አስብበታለው ብላለች፡፡



Image Source: AI

ወጣቷ አያይዛም እኔ መናገር ስለምችል የሚያጋጥመኝ ችግር ከሌሎቹ ይሻላል መናገር የማይችሉት በተለይ ሲወለዱ መስማት የተሳናቸው ለሆኑ ግን ስቃያቸው ከባድ በማለት መስማት መሳንነት በራሷና በሌሎች ላይ የፈጠረውን ተጽሕኖ በሃዘኔታ ገልጻለች፡፡ ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ ታዬ አለምነው "ጠይቄ የገባሁበት አውቶብስ የማላውቀው ቦታ ስላወረደኝ ሆቴል አድሬ በማግስቱ ጠያይቄ ወደቤቴ ሄጃለው" በማለት በሃዘኔታ ተናግረዋል አክለውም በትራንስፖርት የሚያጋጥመኝ ይህ ብቻ አይደለም የሚሉት አንድ ቀን ሳሪስ የሚል ፅሁፍ ያለበት ባስ አይቼ ገባሁና ስልኬን አውጥቼ አዳዲስ መረጃዎችን ስመለከት መልዕቶችን ስጻጻፍ ቆይቼ ቀና ስል ለካ ባሱ በሌላ አቅጣጫ ነው የሚሄደው እኔም "የት ነው ሳሪስ ነኝ የምሄደው ብላቸው ጦር ኃሎች አልፏል ሳሪስ ከሆነ እዚህ አይቆምም ብለው ጋርመንት" አውርደውኛል በማለት በሕዝብ መገልገያ የደረሰባቸውን በደል በምሬት ገልጸዋል፡፡

ከሕዝብ መገልገያዎች ጋር ተያይዞ መስማት የተሳናቸው ሴት እህቶቻችን በትምህርታቸው የሚያጋጥማቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው ? በማለት ለቀረበው ጥያቄ ምላሹን የሰጠ የጥቁር አንበሳ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ቴዎድሮስ አሊ "በቤት ውስጥ የስራ ጫና መብዛቱ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ከፍተኛ የሆነ ተጽህኖ ፈጥሮባቸዋል" የሚለው መምህር አንዳንድ የመስማት የተሳናቸው ወላጆች የልጃቸው መማር የትም ደረጃ እንደማያደርስ በማሰብ አብዛኛውን የቤት ውሰጥ ስራ ለእነሱ በመተው ውድ የጥናት ጊዜያቸውን እንደሚሻሙባቸው ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው መ/ር ተፈሪ ግዛው በምልክት ቋንቋ የሚያስተምራቸው ት/ቤት በአካባቢያቸው ስለማይገኝ ት/ም ፍለጋ ከቤተሰብ ይለያሉ ዘመድ ቤት ተቀምጠው ቢማሩ እንኳ የስራ ጫናው ፣ የአስገድዶ መደፈር ሰለባው ፣ የምግብ ዕጦቱ ፣ የንህፅና መጠበቂያ ማጣቱ . በትምህርታቸው ላይ ተጽሕኖ እንደሚያመጣ አስረድተዋል፡፡

ሌላኛዋ የየካቲት 23 ልዩ ፍላጎት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህር የሆነችው እየሩስ ግርማ "አጠቃላይ የትምህርት ስርዓቱ መስማት የተሳናቸውን ታሳቢ ያደረገ ባለመሆኑ ገና በልጅነታቸው በትምህርት ጉዟቸው ፈተናዎችን ለመጋፈጥ ተዳርገዋል" በማለት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ያሉበትን ሁኔታ ከሙያዋ አንጻር ገልጻልች መምህሯ አያይዛም ምልክት ቋንቋ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ አለመካተት ፤ መስማት የተሳናቸውን የሚያስተምሩ ት/ቤቶች ቁጥር እጅግ

አናሳ መሆን ፤ ምልክት ቋንቋ የማይችሉ መምህራኖች መስማት የተሰናቸውን እንዲያስተምሩ መደረግ ፤ ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠር ሕጻናትን በአካቶ ማስተማርና ሌሎች ያልተጠቀሱ በርካታ ችግሮች በወደፊቱ ትምህርት ጉዟቸው አስቸጋሪ በተለይ ለሴት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ፈታኝ እንደሚሆንባቸው በመግለጽ ትምህርት







ሚኒስቴር ልዩ ድጋፍና ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ከሚመለከታቸው ጋር በመወያየት ዘላቂ መፍትሔ እንዲያበጅላቸው አስታውቃለች። እንደመምህሯ አገላለጽ ከሆነ በሃገሪቱ እየተሰጠ ያለው መስማት የተሳናቸውን ያስተማር ተግባር በበላይ አካል በሚመራ እቅድ ወጥቶለት ቁጥጥር ክትትል የሚደረግለት ሳይሆን ት/ቤቶች በራሳቸው መልካም ፍቃድ እንዲሁም መስማት የተሳናቸውን በማካተት በተቻላው አቅም የሚያደርጉት ጥረት መሆኑ ነው ይህ ደግሞ ቀጣይነት ድጋፍ እንዳያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ ት/ቤቶች ወጥነት የለው አሰራር ለመተግበር ሙያዊ እገዛ የሚያደርግላቸው ስርዓት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል።

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉበት ችግር ለማስወጣት እንደ መምህር ምን ጥረት አድርጋችኋ ? በማለት ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሻቸውን የሰጡን የልዩ ፍላጎት ባለሙያ የሆኑት መ/ር ተፈሪ ግዛው ከዚህ በፊት የተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት ድጋፍ በማሰባሰብ ትራንስፖርት ከፍለው መምጣት ለማይችሉ በተለይ ለሴት

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን እንዲማሩ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም በዚህ ዓመት ግን ድጋፉ መቀጠል ስላልቻለ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ትምህርታቸወን ለማቋረጥ እንደተገደዱ ገልጸዋል። በተመሳሳይ የብሔራዊ ማሕበሩ ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ገዳሙ ሁንዴቻ ማሕበሩ ከሚመለከታቸው አካላት እንደ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ትምህርት ሚኒስቴር መስማት የተሳናቸው ያሉበትን የተግባቦት ችግሮች በማሳወቅ ግንዛቤ በመፍጠር ተካታች እንዲሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያስገነዝባል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

> ”
> የትምህርት ስርዓቱ መስማት የተሰናቸውን ታሳቢ ያደረገ ባለመሆኑ ገና በልጅነታቸው በትምህርት ጉዟቸው ፈተናዎችን ለመጋፈጥ ይዳረጋሉ።

ከአዲስ አበባ ጫፍ ጫፍ ለሚመጡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ባቅራቢያቸው ባሉ ት/ቤቶች ተካተው እንዲማሩ ብሔራዊ ማሕበሩ ምን ጥረት አድርጓል ? ለሚል ጥያቄ ምላሽ የሰጡት የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማሕበር ፕሬዘዳንት ዮሐንስ ተኽላይ አሁን ላይ በአዲስ አበባ ብዙም ጥረት ባይደረግም መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ተቀብለው በአግባቡ ማስተማር የሚችሉ አካቶ ት/ቤቶች በየቦታው ስለማይገኙ ያሉትም ውሱን ት/ቤቶች ክፍተት ስለሚታይባቸው የእነሱን አቅም ሳያጠናክሩ ወደሌላ ቦታ መሄዱ ውጤታማ ሊያደርግ ስለማያስችል ወደፊት እቅድ ተይዞለት ከሚመለከታቸው ጋር ለመስራት ጥረት እናድጋለን በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል::



በዚህ የምርመራ ዘገባ መስማት የተሳናቸው በአካባቢያቸው ምን ችግሮች ያጋጥማቸዋል ? ለሚል ጥያቄ ለቀረበለት ወጣት አረፋይኔ ተስፋዬ “በቋንቋ አለመግባባት ከማሕበራዊ *ህብረት ራስን የማግለል ሁኔታ አለ ” እንደ እቁብ እድር ወይም በኢንተርፕራይዞች ተደራጅቶ ለመስራት ቢፈልጉ አይሰሙም እያሉ መጠቋቆሚያ ቢያደርጉንስ በሚል ፍራቻ ራሳቸውን ከተለያዩ ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች የሚያገሉ መስማት የተሳናቸው እህቶቻችን እንዳሉ ተናግሯል::

“መስማት የተሳናቸው ተከራይተው እንዳይኖሩ የሚያደርጉ አከራዮች አሉ” የምትለው መ/ርት ሕሊና ሳሙኤል ከፍለው ሊከራዩ የመጡትን መስማት የተሳናቸው በመሆናቸው ምክንያት እንደዚህ አይነት ሰው አናከራይም በማለት የሚከለክሉ እንዳሉ ጠቅሳለች::

አንድ ስሟ እንዲጠቀስ ያልፈለገች መላሽ አንዳንድ አከራዮች ሴት መስማት የተሳናቸውን ካልፈጸምን ኪራይ እንጨምርብሻለን ወይ እናስወጣሻለን በማለት ላልተገባ ጫና ውስጥ እንደሚከቷቸው ትናገራለች::

መስማት የተሳናቸው እድሉን ካገኙ እንደማንኛውም ስው ሰርተው መኖር ሚችሉ “ከራሳቸው አልፈው ለሃገር መትረፍ እንደሚችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት ይቀራሉ::

ለምንድነው መስማት የተሳናቸው ተከራይተው እንዳይኖሩ የሚከለክሉት ? ለሚለው ጥያቄ ወ/ሮ ሚሚ ወርቁ እንዳሉት መስማት ካልቻሉ ምን ሰርተው ነው ኪራይ የሚከፍሉት የሚሉ አከራዮች መኖራቸው ሲሆን መስማት የተሳናቸው እድሉን ካገኙ እንደማንኛውም ስው ሰርተው መኖር ሚችሉ “ከራሳቸው አልፈው ለሃገር መትረፍ እንደሚችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት ይቀራሉ” በማለት የመለሱት ወ/ሮ ሚሚ ትኩረት ለሚገባቸው ሴት እህቶቻችን ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እድሎችና ምቹ ሁኔታ በማመቻቸት መስማት የተሳናቸው ለሃገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ መንግስትም

ይሁን የግሉ ዘርፍ አገራችን የተቀበለቻቸውን አለምአቀፍ የአካታችነት ሕጎች በመከተል ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማለት አስተያየቷን ሰጥታለች።

ሃገራችን ኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ሴቶችን ያማከሉ ወርቃማ የሆኑ ሃገራዊና አለምአቀፋዊ ሕጎች ቢኖራትም በአፈጻጸም ረገድ ክፍተቶች ስለሚስተዋሉ ችግሩ ሰር ሰዶ እንዳይገባ በበላይ አካላት ጠንከር ያለ ቁጥጥርና ክትትል ያሻቸዋል የመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰቦችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋሙ ማሕበራት የማሕበረሰቡ የሕልውና ጥያቄ የሆነውን ምልክት ቋንቋ እውቅና እንዲሰጠው መንግስት ላይ ግፊት በመፍጠር ቋንቋውን የስራ ቋንቋ ከማስደረግ በተጨማሪ ሃገሪቱ ውስጥ ባሉ ፕሮግራሞች አካቶ ተግባራዊ በማድረግ የተጣለባቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል።

በጾታዊ ጥቃት ተያይዞ እየተንሰራፋ የመጠው አለመስማትን መሰረት ያደረገ ጾታዊ ጥቃት በመከላከል ረገድ ሁሉም ሕብረተሰብ በመረባረብ አጥፊዎች ላይ የማያዳግም ቅጣት በመስጠት ለሌሎች ማስተማሪያ እንደሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም የመስማት የተሳናቸው ማሕበረሰብ ልዩ መብት የሆነውን የምልክት ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት እንደ አንድ ስራ ዘርፍ በተቋማቸው በማካተት መስማት የተሳናቸው ተገልጋዮች ለማናቸውም ጉዳይ አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ በአስተርጓሚ እንዲስተናገዱ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል መንግስትም የመስማት የተሳናቸውን አቅም ችሎታ በመጠቀም መስማት የተሳናቸው ለሃገራቸው እድገት የድሻቸውን አስተዋጾኦ እንደያበረክቱ ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም ማሕበረሰቡን የሚመለከት ጉዳዮች በኃላፊነት እንዲመሩ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት እስከ ወረዳ ባሉ ተቋማት ያስቀጥራቸው የሚያስችል ኮታ በመመደብ የመስማት የተሳናቸው እኩልነት እንዲረጋገጥ ሰብዓዊ መብት እንዲከብር ተደራሽነት እንዲሰፍን ቀዳሚውን ተግባር ሊፈጽምና ሊያስፈጽም ይገባል።

## ስለ አዘጋጁ



የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ጋዜጠኛና መምህር ናትናኤል ሸፈራው ይባላል በማንጅራት ገትር ሕመም ሳቢያ 11 ዓመቱ መስማት የተሳነው ሆነ። ትምህርቱን ከAAU አጠናቋል።

በአሁኑ ወቅት በመምህርነት እንዲሁም በፋና ቲቪ በጋዜጠኝነት DCDO የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት አቋቁሞ በስራ መሪነት እያገለገለ ይገኛል።

09-25-49-23-43

ጥራት ያለው ትምህርት መስማት
ለተሳናቸው ታዳጊ ሴቶች፡ መብት
እንጂ ችሮታ አይደለም!

# Quality Education for Deaf Girls: A Right,

# Not a Privilege!






# በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የጎለበተ የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ፕሮጀክት

ሀብታሙ ተ/ሰፈራ፣ስነሻው ለገሰ፣መሰረት በለድ እና አርሴማ ማንደፍሮ

## መግቢያ

መግባባት ለሰው ልጅ ህልውና ቁልፍ እንደመሆኑ መጠን እኛ ፍጡራን ማህበረሰብ በመገንባት እና አብሮ በመስራት የተወሰንን ነን። ለዚህም መግባባት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይሁን እንጂ መግባባት ከተስተጓጎለ ሊያጋጥሙን የሚችሉ እንቅፋቶች ብዙ ናቸው።

መስማት የተሳናቸው ሰዎች በትምህርት፣ በጤና፣ በሙያ እና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የተለያዩ እንቅፋቶች ያጋጥሟቸዋል። በሀገራችን መስማት ለተሳናቸው ዜጎች የምልክት ቋንቋ ዋና የመግባቢያ መንገድ ነው። ይሁን እንጂ መፍትሔ ቢሰጥም መስማት በተሳናቸው እና መስማት በሚችሉ ግለሰቦች መካከል ግንኙነት በመፍጠር ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ።

ይህንን ችግር በመቅረፍ መስማት በተሳናቸው እና መስማት በሚችሉ ሰዎች ዘንድ ሁሉን ያካተተ የመግባቢያ ሥርዓት ለመገንባት የቴክኖሎጂ እድገቶችን እና ትክክለኛ መረጃዎችን ማዋሃድ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ አገሮች ከሚነገሩ ቋንቋዎች በተለየ የራሳቸውን የምልክት ቋንቋ ይጠቀማሉ፣ ይህም እንደየሀገራቱ እና እንደየባህላቸው ይለያያል።

በምልክት ቋንቋ እውቅና ላይ ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶች በዋነኝነት በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ ( ASL) ላይ ያተኮሩ ናቸው። በኮንቮሉሽናል የነርቭ አውታረመረብ (CNN) ላይ የተመሰረቱ አቀራረቦች በምልክት ቋንቋ ምደባ ላይ ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን ያሳያሉ። ይሁን እንጂ በአማርኛ የምልክት ቋንቋ ላይ የተደረጉ ምርምሮች ውስን ናቸው።

# የፕሮጀክቱ አላማ ምንድን ነው?

የፕሮጀክቱ ዓላማ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የጎለበተ የአማርኛ ምልክት ቋንቋ ተርጓሚ በመገንባት፣ የኮንቮልሽን የነርቭ አውታረ መረቦችን ( CNN) እና ጥልቅ የመማር ቴክኒኮችን በመጠቀም ይህንን ችግር መፍታት ነው:: ሞዴላችን ከአማርኛ ፊደላት ጋር የሚዛመዱ የእጅ ምልክቶችን ለመለየት የሰለጠነ ነው:: አንድ ምልክት የትኛውን ፊደል እንደሚወክል በመተንበይ ያለውን ልዩነት ይገልጻል::

ይህ ከተስፋፋ እና ይበልጥ በተራቀቀ የመረጃ ስብስብ ላይ ከተተገበረ እንደ ትምህርት እና የጤና እንክብካቤ ባሉ ሰፊ ዘርፎች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል:: ከቴክኒካዊ ስኬቶች ባሻገር ፕሮጀክቱ ማህበራዊ ተጽዕኖን እና ተደራሽነትን በማቀላጠፍ ረገድ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ሚና ያሳያል:: ይህ ፕሮጀክት አንድም ድምፅ ሳይሰማ የማይቀርበት ዘመን ለመፍጠር ትንሹ እና የመጀመሪያው እርምጃ ነው::


# የአሰራር ዘዴው ምን ይመስላል?

በዚህ ጥናት ቀደም ሲል የተሰበሰበውን የአማርኛ ምልክት ቋንቋ ( AmSL) ምስል ማከማቻ ተጠቅመናል:: የውሂብ ስብስቡ የ10 የአማርኛ የምልክት ቋንቋዎችና ትምህርቶች፣ የማይንቀሳቀስ የእጅ ምልክቶች እና ምስሎችን የያዘ ሲሆን በተናጠል የስልጠና እና የሙከራ ስብስቦችን በተዛማጅ የ CSV ማስታወሻዎች አቅርቧል::

የአስተያየት ፋይሎች የድንበር ሣጥኖችን እና የክፍል መለያዎችን ይገልጻሉ:: የውሂብ ስብስቦቹን ወጥነት እንዲኖራቸው ለማድረግ በ 1280 x 720 ፒክስል ጥራት 2,161 የተሰየሙ ምስሎችን የያዘ አንድ ወጥ ስብስብ ውስጥ ተዋህደዋል:: የጥራት ፍተሻዎች የጎደሉ መለያዎች፣ ልክ ያልሆኑ የድንበር ሳጥኖች ወይም የተባዙ መዝገቦች አለመኖራቸውን አረጋግጠዋል::

# የመረጃ ቅድመ ዝግጅቱ ምን ይመስላል?

ከሞዴል ስልጠና በፊት የመረጃ ስብስቡ ለሞዴሉ ተስማሚ እና ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የተወሰኑ የቅድመ ማቀነባበሪያ እርምጃዎች ተተግብረዋል:: በመጀመሪያ ቅድመ ሙከራ ሁሉም ምስሎች ወደ 128 x 128 ፒክስል ወጥ የሆነ ጥራት ተለውጠዋል:: በዚህም የኮንቮልሽን የነርቭ አውታረመረብ ( CNN) ስሌት ቀለል አድርጎታል::



(a)



(b)


መጠኑን ከቀየረ በኋላ የፒክስል ዕሴቶቹ እያንዳንዱን እሴት በ 255 ( ለ8 ቢት ምስሎች ከፍተኛው የፒክስል እሴት) በመከፋፈል ወደ [ 0, 1] ክልል ተስተካክለዋል:: በመደበኛነት ደረጃ ላይ የተመሰረቱ የማመቻቸት ቴክኒኮችን መቀላቀል ያፋጥናል እንዲሁም በስልጠናው ሂደት ውስጥ የቁጥር አለመረጋጋት እድሎችን ይቀንሳል::

ከመጠን በላይ የመገጣጠም አደጋን ለመቀነስ የውሂብ ማጎልበቻ ቴክኒኮችን ተግባራዊ አድርገናል:: እነዚህ እንደ ማዞሪያዎች፣ ስፋት እና ቁመት ሽግግሮች፣ ማጉላት እና አግድም ማዞር ያሉ ጂኦሜትሪክ ለውጦችን ያካትታሉ:: የመረጃ ስብስቡን ብዙሃነት በሰው ሰራሽነት በመጨመር አውታረ መረቡ ሰፋ ላሉ የእጅ ምልክቶች እና የእጅ አቅጣጫዎች ያጋልጣል፣ ይህም የሞዴሉን አጠቃላይ የማድረግ ችሎታ ጨምሮታል::

በተጨማሪም ምድብ ያላቸው መለያዎች በመለያ ኢንኮዲንግ በመጠቀም ወደ ኢንቲጀር ኢንዴክሶች ተለውጠዋል:: በመጨረሻው በሶፍትማክስ ድርብርብ ውስጥ ከአንድ ልዩ የውጤት ክፍል ጋር ይዛመዳል:: ይህ ደረጃ የመረጃ ስብስቡን ከኒውሮል አውታረመረብ መስፈርቶች ጋር ለማጣጣም አስፈላጊ ነበር::.

## ሞዴል አርክቴክቸር

ለምስል ምደባ ጥልቅ የመማሪያ ክዋኔያዊ የነርቭ አውታረመረብ ( ሲኤንኤን) ተግባራዊ አድርገናል። አውታረ መረቡ የ 128 x 128 x 3 መጠን ያላቸውን የግብዓት ምስሎችን ይወስዳል። ሞዴሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ ማጣሪያዎችን ( 32, 64 እና 128) የያዘ ሦስት የሽብልቅ ንብርብሮችን ያቀፈ ነው።




እያንዳንዱ የሽብልቅ ንብርብር የ 3 x 3 ኮርኔል፣ የተስተካከለ መስመራዊ አሐድ ተግባር እና ልኬትን ለመቀነስ እና በጣም አስፈላጊ ባህሪያትን ለመያዝ የ 2 x 2 ከፍተኛ-የመደመር ንብርብር ይጠቀማል። ከኮንቮልሽናል ንብርብሮች በኋላ የባህሪ ካርታዎች ወደ አንድ-ልኬት ቬክተር ጠፍጣፋ ይሆናሉ።ጠፍጣፋው ውጤት የተስተካከለ መስመራዊ አሐድ (Rectified Linear Unit) በ128 ነርቮች ወደሚይዝ ሙሉ በሙሉ የተገናኘ ጥቅጥቅ ባለ ንብርብር ይተላለፋል።

ይህ ባህሪ ለሞዴሉ የተወሰዱትን ባህሪዎች እንዲያጣምር ይረዳል። ምስሎቹንም ወደ አሥሩ የአማርኛ ምልክት ክፍሎች ለመመደብ የ 10-ኒውሮን ሶፍትማክስ ውፅዓት ድርብርብ ጥቅም ላይ ይውላል። በ ሞዴሉ ውስጥ የሚሰለጥኑ መለኪያዎች ጠቅላላ ቁጥር በግምት 3.,3 ሚሊዮን ነው፣ ይህም ሞዴሉን የእጅ ምልክት ልዩነትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመያዝ የሚያስችል ያደርገዋል።

## የሞዴል ስልጠና

ሞዴሉ የተሠለጠነው በአዳም ማመቻቸት አማካኝነት በ 0.001 የመማር ፍጥነት ሲሆን አነስተኛ ደረጃ ያለው የመስቀል-ኢንትሮፒ እንደ ኪሳራ ተግባር ጥቅም ላይ ውሏል። ስልጠናው የተካሄደው በ32 ምስሎች ስብስብ ላይ እና በ50 ዘመናት ነው። በተጨማሪም ለሦስት ተከታታይ ዘመናት ምንም ተጨማሪ መሻሻል በማይታይበት ጊዜ ስልጠናውን ለማቆም የቅድመ ማቆሚያ ዘዴ ተተግብሯል፣ ይህም ሞዴሉ ከመጠን በላይ እንዳይገጣጠም ከልክሏል።

## የፕሮጀክቱ የግምገማ መለኪያዎች ምንድን ናቸው?

የሞዴሉን አፈጻጸም ለመገምገም እንደ ትክክለኛነት፣ ማስታወስ እና የ F1 ውጤት ያሉ የተለመዱ የግምገማ መለኪያዎችን እንዲሁም ግራ መጋባት ማትሪክስ እና የ ROC-AUC ትንታኔን ተጠቅመናል። እነዚህ መለኪያዎች የስልጠና እና የማረጋገጫ ስብስቦችን ትክክለኛነት እና ኪሳራ ለመገምገም ረድተውናል።

የሞዴል ስልጠናውን ተከትሎ የመጨረሻው ሞዴል ከ Streamlit ድር መተግበሪያ ጋር ለመዋሃድ ተጠብቋል። መተግበሪያው ተጠቃሚዎች የምልክት ምስል እንዲጭኑ

እና ትንበያ እንዲያደርጉ የሚያስችል ቀላል እና ለተጠቃሚ ተስማሚ ነው። ከዋናው ተግባሩ በተጨማሪ መተግበሪያው በርካታ ቋንቋዎችን ይደግፋል፣ አማርኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች አሁን ይገኛሉ።

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚሠራው የአማርኛ ምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ልማትና አተገባበር በኢትዮጵያ የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች የሚያጋጥማቸውን የግንኙነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል ትልቅ እርምጃ ነው። በሙከራ ጊዜ 94.12% እና የመጨረሻ ውጤቱ ደግሞ 98.84% ነው። እነዚህ ጥልቅ የመማር እና የኮምፒተር ራእይ ቴክኒኮች የደረሱበትን ጥልቀት ያሳያሉ።

እንዲህ ዓይነቱን አፈጻጸም ማግኘቱ አገልግሎት ባልተሟሉ ክልሎች ውስጥ የቋንቋ እና ተደራሽነት ክፍተቶችን ለማስተካከል የAI አቅምን ያሳያል። ለምርምር ተብሎ ከተዘጋጀው ፕሮቶታይፕ መፍትሄው በድር ጣቢያ በኩል የተጠቃሚ በይነገጽ በመገንባት ወደ ተግባራዊነት ተሻሽሏል።

## የፕሮጀክቱ ስኬት

በ Frontier Tech Leaders Programme Machine Learning Bootcamp ውድድር 2ኛ ደረጃን በማሸነፍ በእውነተኛው ዓለም ውስጥ ስላለው የፈጠራ ችሎታ እና አጠቃቀም ብዙ ይናገራል።

ዓላማችን ፕሮጀክቱን ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር በማገናኘት የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ ነው። ይህም ሁሉን ያካተተ የመማሪያ አከባቢዎች አስፈላጊ ሀብት ሊሆን ይችላል። ለአማርኛ የምልክት ቋንቋ የተዘጋጀው ባህላዊ እና አውደ-ጽሑፋዊ ተጋላጭነት ሰው ሠራሽ የማሰብ ችሎታ አካባቢያዊ አተገባበርም ቅድመ ሁኔታን ይፈጥራል። ሆኖም ወደ ሌሎች ቋንቋዎች የማስፋፋት እሳቤዎች አሉ። ነገር ግን እንደ የውሂብ ስብስብ ገደቦች እና የእውነተኛ ጊዜ ማቀነባበሪያ መስፈርቶች አስፈላጊነት ያሉ ገጽታዎች ማጣራት የሚፈለግባቸውን አካባቢዎች እንዳዱዱ ያመለክታሉ።

## በቀጣዩ ሊሰሩ የታሰቡ ስራዎች ምን ይመስሳሉ?

በርካታ አማራጭ ማራዘሚያዎች ይታያሉ። በመጀመሪያ፣ የመረጃ ስብስቡ የሞዴሉን የተሻለ አጠቃላይነት ለማስቻል ሰፋ ያለ የእጅ ምልክቶችን ለማካተት ይሞከራል። አሁን ይህ የተለያየ የተጠቃሚ ግብአት ተገዢ በሚሆንበት ጊዜ ለትክክለኛነቱ የተሻለ መለኪያ ይሰጣል።

ትምህርት ቤቶችን እና ተቋማትን በመቀላቀል በመማሪያ መርሃ ግብሮች ውስጥ መሣሪያውን በማካተት እና አስተማሪዎችን በማካተት የመማሪያ ክፍሎችን በመደገፍ ከትምህርት ሥርዓት ጋር ያለውን ውህደት ማራመድ ሌላው ቁልፍ ትኩረት ይሆናል። ትክክለኛነቱን እና ተቀባይነቱን ለማረጋገጥ ከአካባቢያዊ ማህበረሰቦች እና ባለሙያዎች ጋር መተባበር በጣም አስፈላጊ ነው።

የረጅም ጊዜ ግብ ተግባራት ሥርዓቱን ከብስለት ቴክኖሎጂዎች ወይም ለትላልቅ ታዳሚዎች የሞባይል መድረክን ማዋሃድ ያካትታሉ። የተጠቃሚዎችን ግላዊነት እና አድልዎ ቅነሳን ጨምሮ በሥነ-ምግባራዊ የአይ ኤስ ማሰማራት ላይ ቀጣይነት ያለው ምርምር የወደፊት ድግግሞሾችን ይመራል። መፍትሄው አካታች እና ፍትሃዊ ሆኖ እንዲቆይ ያደርጋል።

## የፕሮጀክቱ ውጤት ምን ይመስላል?


የአማርኛ የምልክት ቋንቋን እውቅና ለመስጠት የተቋቋመው የነርቭ አውታረ መረቦችን( CNN) ግምገማ እንዳንድ አስደናቂ ውጤቶችን ያገኘ ሲሆን የሞዴሉን ጠቃሚነት መገንዘብ ተችሏል። አፈጻጸሙ የተገመገመው የሞዴሉን የመማር ችሎታ እና አጠቃላይ ኃይሉን ለማረጋገጥ የሙከራ ስብስቦችን መጠቀም ተችሏል።

በተረጋገጠ ስብስብ ላይ ሞዴሉ 98.84% ትክክለኛነት አግኝቷል፣ ይህ ማለት በተረጋገጠ ስብስብ ውስጥ


ያሉትን የእጅ ምልክቶች ክፍሎች በመመደብ አጅግ የላቀ ችሎታ አሳይቷል። እንዲህ ዓይነቱ ትክክለኛነት ሞዴሉ የሰለጠነባቸውን ባህሪዎች የመመደብ ችሎታን የሚያንጸባርቅ ነው። ይህ ፕሮጀክት 94.12% የሙከራ ትክክለኛነት አግኝቷል፣ ይህም ሞዴሉ ሙሉ በሙሉ አዲስ በሆነ የውሂብ ስብስብ ላይ እንዴት እንደሚሠራ ያሳያል።

## ቁልፍ ግኝቶች እና መደምደሚያዎች

ከሜትሪክ መለኪያዎች ባሻገር በ ሞዴሉ ስልጠና እና ግምገማ ወቅት የተደረጉ አንዳንድ ትኩረት የሚስቡ ምልከታዎች ነበሩ። አስፈላጊ የሆኑ ምልከታዎች ሞዴሉ ከመጠን በላይ የመገጣጠም ( Overfitting) ምልክቶችን አያሳይም። ከመጠን በላይ የመገጣጠም (Overfitting) የሚከሰተው ሞዴል ከስልጠናው ስብስብ ጋር ከመጠን በላይ በሚስማማበት ጊዜ ሲሆን ይህም በአዳዲስ መረጃዎች ላይ አፈጻጸሙ እንዲበላሽ ያደርገዋል።




ቀደም ብሎ ማቆም በቀጥታ ይህንን ስኬት ያረጋግጣል፣ ምክንያቱም በማረጋገጫ ስብስብ ላይ የሞዴሉ አፈጻጸም መሻሻል ሲያቆም ወይም መበላሸት ሲጀምር ስልጠናውን ያቆማል። የዚህ በማረጋገጫ እና በሙከራ ትክክለኛነት መካከል ያለው ትንሽ ልዩነት ሞዴሉ አጠቃላይ የማድረግ ችሎታ እንዳለው የሚያረጋግጥ ነው። ከትክክለኛነት ጎን ለጎን የሞዴሉ አፈጻጸም በኪሳራ ዕሴቶች ተገምግሟል፣ ይህም የትንበያዎችን የስህተት መጠን ይለካል።የተመዘገበው ስህተት 0.0711 ሲሆን የፈተናው ኪሳራ 0.1709 ነው።




እነዚህ ዝቅተኛ እሴቶች ከትክክለኛ ውጤቶች ጋር ይዛመዳሉ፣ ይህም ሞዴሉ በደንብ የሰለጠነ መሆኑን ያሳያል። በተጨባጭ የኪሣራ እሴት በጣም ዝቅተኛ መሆን ማለት አብዛኛው የሞዴሉ የተተነበዩ መለያዎች ከእውነተኛ መለያዎች ጋር በቅርበት ይዛመዳሉ ማለት ነው።

ትክክለኛነት፣ በዋናነት የ 94.12% የሙከራ ስብስብ ውጤት ነው፣ ይህም ጠንካራ የእጅ ምልክት ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጫ ሆኖ ያገለግላል።

በመሆኑም ሞዴሉ አስተማማኝ ነው፣ የተሰጡትን የእጅ ምልክቶች ሁልጊዜ በትክክል ይመድባል። እንዲህ ዓይነት ደረጃ ያለው አስተማማኝነት እንደ አማርኛ የምልክት ቋንቋ ትርጉም ባሉ ትግበራዎች ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በአጭሩ ይህ ማዕቀፍ የአማርኛ

የምልክት ቋንቋ ተጠቃሚዎችን የሚያግዝ፣ መሣሪያ በማቋቋም በኢትዮጵያ ዐውድ ውስጥ እንዲካተቱ እና ተደራሽ እንዲሆኑ በመደገፍ ዋና ዓላማችንን እውን ለማድረግ በአዎንታዊ አበርክቶ አለው።


## የፕሮጀክቱ የማጠቃለያ ሃሳብ

ይህ ፕሮጀክት አላማው በኢትዮጵያ መስማት በተሳናቸው እና መስማት በሚችሉ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የመግባባት ክፍተት ለመሙላት በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በመታገዝ የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚን ማዘጋጀት ነው። ፕሮጀክቱም የኮንቮልሽናል የነርቭ አውታረ መረቦችን(CNN)እና ጥልቅ የመማር አቀራረቦችን በመጠቀም ሥርዓቱ በ 98.84% ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና በቅድመ ሙከራ ጊዜ 94.12% ትክክለኛ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። እነዚህ ግኝቶች የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ምልክቶችን ለመለየት ያለውን ጥቅም ያሳያሉ።

ይህ ፕሮጀክት ከቴክኒካል ጥቅሙ ባሻገር እንዴት አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ማህበራዊ ህይወትን እንደሚያበረታታ እንዲሁም ተደራሽነትን እንዴት እንደሚያሳድግ እና የተባበሩት መንግሥታት ዘላቂ የልማት ግቦችን እንዴት እንደሚያራምድ ያሳያል። ምንም እንኳን የትክክለኛ መረጃ ውስንነቶች ቢኖሩም ፕሮቶታይፕ ማሻሻያዎች በእርግጠኝነት የሚደረጉበት ጠንካራ መሠረት ነው።

ለምሳሌ የቪዲዮ ትርጉም ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋዎች ለማስፋፋት፣ በትምህርት እና በጤና ሥርዓቶች ውስጥ ያለውን ውህደት ይጨመራል። ስለዚህ ይህ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ መተግበርያ የቴክኖሎጂው ኢንዱስትሪ የተለያዩ ማህበራዊ ለሆኑ ችግሮች መፍትሄዎችን በማጎልበት ረገድ ልዩነት ሊፈጥር እንደሚችል ያሳያል። የመጨረሻ አላማው እያንዳንዱ የሚነገር እና በምልክት የሚገለጸ ድምጽ እንደሚሰማና ዋጋ እንዳለው ማረጋገጥ ነው።

### ስለ አዘጋጆቹ



ስንሻው ለገሰ በኢትዮጵያ Armauer Hansen Research Institute (AHRI), የመረጃ ሳይንስ ረዳት ተመራማሪ ነዉ።

ነዉ።በኮምፒዩተር ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኮምፒዩተር ዳታ ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪ እያጠና ይገኛል።

መሠረት ቦለድ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የኣምስተኛ አመት የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ተማሪ ናት ።በ fullstack development እና machine learning ልምድ ያላት ስትሆን አሁን ላይ በግዝያዊነት ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ውስጥ እየሠራች ትገኛለች።

አርሴማ ማንደፍሮ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የ4ኛ አመት ባዮሜዲካል ኢንጂነሪንግ ተማሪ ናት። በአርትፊሻል ኢንተለጅንስ እና ማሽን ለርኒንግ ላይ ትልቅ ፍላጎትና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የመስራት ተነሳሽነት አላት።

ሀብታሙ ታደሰ በአሁኑ ጊዜ በኢትሮኒክስ የRobotics እና Autonomous Systems Institute ውስጥ በምርምር እና ልማት መሐንዲስነት ሙሉ ጊዜ ሲሰራ፣ በተመሳሳይ ጊዜ Artificial intelligence እና በ Financial Engineering ድርብ MSc ዲግሪ እየተከታተለ ነው። በተጨማሪም፣ ከAfriDATAi ጋር remotely በቢደኦ አቀናባሪነት ይሰራል።


















“በዝምታ ውስጥ ድምጻችን ይሰማል - ለእሷ ድምጽ ለመሆን አብረን እንጓዛለን”
በሚል መሪ ቃል ጥራት ያለው ትምህርት መስማት ለተሳናቸው ዜጎች እንዲሚገባ
ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተደረገው ሃይኪንግ ፎቶዎች




# የጥንካሬ እና የጽናት ተምሳሌቷ ሴት!

በ ጋሻው ተስፋው

በኢትዮጵያ እና በሌሎች መሰል ታዳጊ በሆኑ የአፍሪካ ሀገራት የመስማት ችግር ያለባቸው ህጻናት በተለይም ልጃገረዶች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በዝምታ ማለፍ የተለመደ ነው፡፡ የዛሬዋ ባለታሪካችን መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶች በትምህርት እና በእኩልነት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ የሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ያሳያል፡፡ የራሄል የህይወት ልምድ በተለይ መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶች በየቀኑ ስለሚኖሩት የጸጥታ ህይወትና የትምህርት ጉዞ አጉልቶ በማሳየት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

ይች ባለታሪካችን ራሄል ክንዴ ትባላለች፡፡ ራሄል በ1993 ዓ.ም በአማራ ክልል ከደብረ ታቦር ከተማ ወጣ ካለች አነስተኛ የገጠር መንደር ተወለደች፡፡ እድገቷም በዚያው ነው፡፡ ከተወለደችበት ጊዜ ጀምሮ የመስማት ችግር አልነበራትም፡፡ ሙሉ በሙሉ መስማት እና እንደማንኛውም ልጅ መግባባት ትችል ነበር፡፡

ራሄል በህይወቷ የመጀመሪያዎቹን ስምንት ዓመታት ያለምንም የመስማት ችግር ኖራለች፡፡ ይሁን እንጂ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በህመም ምክንያት በሁለቱም ጆሮዎች ላይ የመስማት ችሎታ ቀስ በቀስ እንደጠፋ ትናገራለች፡፡ ራሄል መደበኛ ትምህርቷን ከመጀመሯ በፊት ያደገችው በገጠር ሲሆን የቤተሰቦቿ አኗኗር በግብርና ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡

ራሄል እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት ትምህርቷን ለመጀመር ከትውልድ መንደሯ አቅራቢያ ወደሚገኝ የአውራጃ ማእከል ከተማ እንደመጣች ትናገራለች፡፡ ‘‘መጀመሪያ ትምህርት ቤት የገባሁባት ትንሽ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት ነበረች’’ ከዛም በኋላ ስለ ጉዳዩ በደስታ ተናገራለች፡፡ ራሄል ለአራት ተከታታይ ዓመታት ማለትም ከ1ኛ ክፍል እስከ 4ኛ ክፍል በምልክት ቋንቋ በመማር እና በመከታተል ጥሩ ውጤት እንዳስመዘገበች ትገልፃለች፡፡

በበክፍል ውስጥ በምትማርበት ሰአት ራሄል ከአስተርጓሚዎቿ እና ከፊል ከሚሰሙ የክፍል ጓደኞቿ ጋር በደስታ በመግባባት ብዙ ልምዶችን ወስዳለች። ይህንን ወቅት አስደሳች የፍቅር ጊዜ ነበር በማለት ታስታውሳለች።




Image Source: www.kentalis.com

ራሄል በትንሿ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍልን ካጠናቀቀች በኋላ በጥሩ ውጤት ወደ 5ኛ ክፍል ተዘዋውራለች። ሆኖም ግን እንደበፊቱ የክፍል ውስጥ ያሉ አስተርጓሚዎች ማግኘት አልቻለችም። ራሄል ይህ የሆነው በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ የትምህርት ዓይነቶች በመጨመሩ በአስተርጓሚ እጥረት ምክንያት እንደሆነ ገልጻለች።

ይህ ሆኖ ግን ራሄል ለመማር ያላትን ፍቅር እና ስኬታማ ለመሆን ያላትን ቁርጠኝነት ወደኋላ ከመተው ይልቅ ወደፊት በመገስገስ አጠናክራ ቀጥላለች። በዚህም ራሄል ባገኘችው እድልና ድጋፍ በመጠቀም ትምህርቷን ለመቀጠልም ትወስናለች። በክፍል ውስጥ የአስተርጓሚ ድጋፍ ባይኖራትም የመማሪያ መጽሃፍቶችን፣ የመምህራኑን ጽሁፎች ከጥቁር ሰሌዳ ላይ በጥንቃቄ በመመልከት እና በማስታወሻ በመጻፍ ይዘቱን ለመቅሰም እና ትምህርቷን ለመከታተል ያላትን ሁሉ ዘዴዎች በመጠቀም ያለማንም ድጋፍ በራሷ ነገሮችን ማቅለል እንደቻለች ገልጻለች። በዚህም በትምህርቷ ጥሩ ውጤት ማምጣት ችላለች።

ራሄል ከክፍል ጓደኞቿ ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረቷንና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከእነሱ መረጃዎችን በማግኘት ያለስጋት መከታተል መቻሏንም ታነሳለች ። ከእኩዮቿ ጋር አብሮ መስራትን፣ መረጃን በመካፈል እና ከእነሱ ጎን ለጎን በትምህርቷ አብራቸው ወደፊት መገስገሷን ትገልጻለች። በዚህ ቁርጠኝነት ራሄል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በጥሩ ውጤት አጠናቃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደርሳለች።

ይህንን በራሷ የራሷን አላማ ማከናወን ወይም ማሳካት በመቻሏ በታላቅ ደስታ ትገልጻለች።

ራሄል ከራሷ ትጋትና ልምድ በተጨማሪ የማመሳከሪያ መጽሐፍትን በመጠቀምና እኩዮቿ ጋር በመማር የከፍተኛ ትምህርቷን ለመከታተል የሚያስፈልጓትን ውጤቶች እንድታገኝ እንዳስቻላት ተናግራለች።

ራሄል በጉዞዋ ሁሉ 12ኛ ክፍልን ካጠናቀቀች እና የሚፈለገውን ውጤት ካገኘች በኋላ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በሚገኝ እንደ MasterCard foundation ከሚባል ድርጅት ነጻ የትምህርት እድል ማግኘቷንና በዚህ ግብረ ሰናይ ድርጅት ብዙ እድሎችን እንደ አጋጣሚ ማግኘቷን ትናገራለች ።ይህ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አካዳሚያዊ እና የግል ህይወቷን በተቀናጀ እና በዘላቂነት እንድትመራ ረድቷታል። በተጨማሪም ራሄል በመረጠችው የትምህርት ክፍል በመግባት በልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍል በድግሪ መመረቋን አስረድታለች።



ራሄል በትምህርት ጉዞዋ ብዙ ችግሮች እና መሰናክሎች እንዳጋጠሟት ትናገራለች። እነዚህ ችግሮች እና መሰናክሎች የዕለት ተዕለት ትግል ብቻ ሳይሆኑ የረጅም ጊዜ ውጊያዎች መዳረሻ፣ የክብር መገለጫ እና የመረዳዳት ውጤቶች እንደነበሩ ተናግራለች። በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ የመገለል ስሜት እና የመግባቢያ ችግሮች ጋር ትታገል እንደነበር ያነሳች ሲሆን ነገር  ግን እነዚህን ፈተናዎች በትዕግስት ተቋቁማለች።

ለመከታተል አስቸጋሪ የሆኑ የአስተማሪ  መልዕክቶችን እና ትምህርቶችን፣ ፈጣን የቦርድ ጽሁፍ ወይም አስተማሪዎች የጻፏችውን እኛ ሳንረዳ ተሎ ማጥፋት ይህም ለመከታተል አስቸጋሪ አድርጎብኛል፣ በፈተና ወቅት ግራ መጋባት፣ ጥያቄዎችን በተሳሳተ መንገድ መተርጎም፣ ተደራሽነት የጎደለው የፈተና አፈታተን፤ አስተራረምና Result አያያዝ ችግር፤ በቡድን እንቅስቃሴዎች ውስጥ ደካማ ተሳትፎ፤ አስፈላጊውን የኮርስ መረጃ የማግኘት ችግር፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለመግባባት መቸገር በክፍል ውስጥ እንቅፋት ሆኖብኝ ነበር ትላለች።

የራሄል ታሪክ የግል ጉዞ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ስርአቱ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ትርጉም ባለው መንገድ ማካተት እንዴት እንዳልቻለ የሚያሳይ ነው። በክፍል ውስጥ የነበራት ዝምታ ምርጫ ሳይሆን የጎደሉ መዋቅሮች ውጤት ነው::: ምንም አስተርጓሚ የለም፣ የሰለጠኑ አስተማሪዎች የሉም፣ አካል ጉዳተኞችን ያካተተ ፖሊሲ የለም። እነዚህ ክፍተቶች እንደማንኛውም ሰው እኩል የመማር መብቷን ጥሶታል።

ሆኖም በዚህ ዝምታ ራሄል ከፍተኛ ውስጣዊ ጥንካሬን አዳብራለች። የእርሷ ታሪክ እንደሚያስተምረን የድጋፍ አለመኖር ችሎታን አያጠፋም። ትንንሽ ክፍተቶችን የመማሪያ መጽሃፎችን ፣ ደግ የክፍል ጓደኞቿን ፣ የራሷን ፍላጎት  የማትረፊያ መሳሪያዎች አድርጋቸዋለች።

ይህ ነጸብራቅ የተግባር ጥሪ ነው። ራሄል በትንሽ ነገር ወደዚህ መሄድ ከቻለች፣ እሷ እና እሷን መሰሎቿ በሙሉ በማካተት ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ እናስበው። ጉዞዋ ከበጎ አድራጎት ወደ ፍትህ፣ ከመራት ወደ እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት እድል እንድንመለከት ያሳስበናል።




"እነዚህን መሰናክሎች እኔ ራሴ አሸንፌ፣ ህልሜ ሌሎች ተመሳሳይ መሰናክሎችን የሚጋፈጡ ሰዎችን መርዳት ነው። በጽናት እና ተቋማዊ ድጋፍ በድል አድራጊነት መወጣት፣ ከቻልኩ  እና አንድ ቀን ሌሎችን ለመደገፍ የሚያስችል ጥንካሬ ካገኘሁ የስኬትን መንገድ ላሳያቸው እችላለሁ "

መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶችን እንደ ተጎጂ ከመመልከት ወደ ለውጥ ፈጣሪነትና ወደ እውቅና የምንሸጋገርበት ጊዜ ነው።



እነዚህ የማያቋርጡ እንቅፋቶች ቢያጋጥሟትም ራሄል በራሷ ውሳኔ እና ባለው ውስን ሃብት ላይ በመተማመን ጸንታለች። ትምህርቷን ለመደገፍ ቤተሰቧ ያደረጉት ጥረት ጉልህ እና ቀላል እንዳልሆነም አበክራ ተናገራለች።

ራሄል በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋም ተመሳሳይ ፈተናዎች ገጥመዋታል። የነፃ ትምህርት ዕድሏ የትምህርት ክፍያን የሚሸፍን እና የተለያዩ እድሎችን የሚያመቻች ቢሆንም፣ የአስተርጓሚ ወይም የምልክት ቋንቋ ድጋፍ እጦት ትልቅ እንቅፋት ሆኖባት እንደቀጠለ ገልጻለች። የቀደሙት ችግሮች አሁንም ይከተሏታል። ከነዚህ ውስጥም ከአዲስ አካባቢ ጋር ለመላመድ፣ ጓደኝነት ለመመሥረት እና የአካዳሚክ ሥርዓቶችን ለመምራት በተለይ የመስማት ችግር ያለበት ተማሪ አስቸጋሪ እንደሆነ አውርታለች።

አክላም ራሄል እንዲህ በማለት ትገልፃለች፣ እያንዳንዱ ክፍል ያልታወቀ ድጋፍ ያልተለመደ ስሜትን አሳድሮብኛል፣ ፍላጎቶችን በማላውቃቸው ፕሮፌሰሮች ለማሟላት መመካት ያለማቋረጥ እራሴን ማስረዳት እንዳለብኝ አስተምሮኛል፣መረጃን የሚለዋወጡበት ስርዓቶች አልነበሩም፣ ከሰዎች ጋር ለመግባባት ግራ የሚያጋባ ነበር፣ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለማስተናገድ ተቋማዊ ድጋፍ ሰጪ መዋቅሮች በአብዛኛው አልነበሩም ትላናለች። ሆኖም ራሄል እነዚህን ተግዳሮቶች በአዎንታዊ መልኩ ለማየት መርጣለች። ተስፋ እንድትቆርጥ ምክንያት ሳይሆን ቆራጥ ውሳኔዋን ለማጠናከር እንደ ማገዶ ቆጥራቸዋለች።

ራሄል ስለወደፊት ምኞቷ እንዲህ ትላለች። “እነዚህን መሰናክሎች እኔ ራሴ አሸንፌ፣ ህልሜ ሌሎች ተመሳሳይ መሰናክሎችን የሚጋፈጡ ሰዎችን መርዳት ነው። በጽናት እና ተቋማዊ ድጋፍ በድል አድራጊነት መወጣት፣ ከቻልኩ እና አንድ ቀን ሌሎችን ለመደገፍ የሚያስችል ጥንካሬ ካገኘሁ የስኬትን መንገድ ላሳያቸው እችላለሁ “ በማለት ምኞቷን ትናገራለች።

በተጨማሪም ራሄል ለዚህ ሁሉ ስኬቷ እንድትበቃ ስላገዟትና ለረዷት ጓደኞቿ፣ መምህራን፣ ወላጆቿና MasterCard Foundation ከፍ ያለ ምስጋናዋን ገልጻለች። በጉዞዋም ሁሉ ላደረጉት ማበረታቻ ምስጋና አቅርባለች።

በተጨማሪም ራሄል በማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ረዳትነት ከተመረቀች በኋላ የስራ እድሎችን በመከታተል በአሁኑ ስአት በማስተር ካርድ ፋውንዴሽን እና The Light of The World በተባለ ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት የስራ እድል አግኝታለች። አሁን ራሄል በጎንደር ከተማም ተመሳሳይ የትምህርት ችግር ያለባቸውን ህጻናትን በመደገፍ በ Grand Assistive Technology (GAT) ሁሉን አቀፍ የቅድመ ልጅነት ልማት እና እንክብካቤ ማዕከል በመስራት ላይ ትገኛለች። ስራ ከጀመረችም አንድ አመት ቆይታ እያደረገች ነው።

ራሄል አሁንም ሌላ የድህረ ምረቃ እድሎችን እየፈለገች ነው። የማስተርስ ዲግሪ አግኝታ በመጨረሻም ፒኤችዲ የመከታተል ህልም አላት። በተደራሽነት እጦት

የኢትዮጵያን ሀገር አቀፍ የድህረ ምረቃ መግቢያ ፈተና መውሰድ ባትችልም ተስፋ አልቆረጠችም። “እዘጋጃለሁ” ትላለችህ። “ እኔ ወደ ውጭ አገር እየተመለከትኩም ነው ትላለች።

የራሄል ታሪክ የሚያሳየው የአንድ ሴት ልጅ በችግር ላይ ስላደረገችው ድል ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ብዙ መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶች የተሞክሮ ነፀብራቅ ነው። የእርሷ ጉዞ አሳታፊ የትምህርት ሥርዓቶችን፣ ተደራሽ የትምህርት አካባቢዎችን እና ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ጠንካራ ተቋማዊ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ነው። በእሷ ጥንካሬ እና ጽናት ራሄል የተስፋ እና የይቻላል ምልክት ሆናለች። ራሄል ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስተማሪዎች እና ማህበረሰቦች ትርጉም ያለው እርምጃ እንዲወስዱ ትጠይቃለች።

## ስለ አዘጋጁ



የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ጋሻው ተስፋው ይባላል። በማንነቱ መስማት የተሳነው  ሲሆን ከጎንደር ዩኒቨርሰቲ የመጀመሪያ ድግሪውን በማኔጅመንት ትምህርት ክፍል አግኝቷል።

በአሁኑ ግዜ ጋሻው በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ አካል ጉዳተኞችን በመወከል የሙያ ዕድገት ስልጠናን በመስጠትና በማሰልጠን ላይ ይገኛል።

09-08-08-63-41

# እጆች ሲናገሩ
# ዓለም ያዳምጣል!

#HandsSpeakEyesListen
#እጆች_ይናገራሉ_አይኖች_ያዳምጣሉ